# የወላጅ መመሪያ

## ለልጅ ጥበቃ አገልግሎቶች (ሲፒኤስ)



የልጆች አስተዳደር

የልጆችና ቤተሰብ አገልግሎት ክፍል

# ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| የልጅ ጠባቂ አገልግሎት (ሲፒኤስ) ምንድን ነው? | 2 |
| የልጅ መጎሳቆልና በቸልተኝነት መያዝ ምንድን ነው? | 2 |
| ስለ እኔ ሲፒኤስ የሰማው እንዴት ነው? | 3 |
| ለልጄ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ሲፒኤስ ምን መብት አለው? | 3 |
| ፖሊስ በጉዳዩ የሚገባው መቼ ነው? | 4 |
| "የአደራ ጠባቂ" ምንድን ነው? | 5 |
| ልጄ ለአደራ ጠባቂ ሲሰጥ ምንድን ይሆናል? | 5 |
| ለእኔና ለቤተሰቤ የሚቀርቡ አገልግሎቶች ምንድን ናቸው? | 6 |
| አማራጭ እርዳታ መስጪያ ዘዴ (ኤአርኤስ) ምንድን ነው? | 7 |
| ሲፒኤስ በሚመረምረኝ ጊዜ ያሉኝ መብቶች ምንድን ናቸው? | 8 |
| ሲፒኤስ ጉዳዩን በሚከታተልበት መንገድ ካልተስማማሁ መብቶቼ ምንድን ናቸው? | 9 |
| ከመኖሪያ ቤት ውጭ ምደባ ምንድን ነው? | 10 |
| "ጥገኝነት" ምንድን ነው? | 11 |
| ወላጅ እንደመሆኤ ልጄ ከመኖሪያ ቤቱ ውጭ ለሚደረግለት ጥበቃ ከተመደበ ወይም ጥገኛ መሆኑ ከታወቀ ያሉኝ መብቶች ምንድን ናቸው? | 11 |
| የልጄ መብቶች ምንድን ናቸው? | 13 |
| ከእኔ የሚጠበቀው ምንድን ነው? | 13 |
| ልጄን መልሼ ማግኘት የምችለው እንዴት ነው? | 14 |
| ጠበቃ ያስፈልገኛልን? | 15 |
| ለልጄ የወደፊት ኑሮ ዕቅድ የማወጣው እንዴት ነው? | 16 |
| "የወላጅነት መብቶች መቀም" ምንድን ነው? | 17 |
| በጉዳዩ ውሳኔዎች ላይ ከሲፒኤስ ጉዳይ አስፈፃሚ ጋር ስምምነት ካልተደረሰ አንድ ግለሰብ ምን ማድረግ ይችላል? | 18 |
| አንድ ግለሰብ ተጨማሪ መረጃዎች የሚያገኘው ከየት ነው? | 18 |
| ልዩነት ያለማድረግ ፖሊሲ | 19 |

## የልጅ ጠባቂ አገልግሎት (ሲፒኤስ) ምንድን ነው?

ሲፒኤስ በሕብረተሰብና ጤና አገልግሎቶች ጽ/ቤት (ዲኤስኤችኤስ) በልጆችና ቤተሰብ አገልግሎት ክፍል (ዲሲኤፍኤስ) ውስጥ ያሉ ሠራተኞች ከሚሠሯቸው ሥራዎች ውስጥ አንዱ ነው። ሲፒኤስ ልጆችን ከመጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት ከመያዝ የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት።

የሲፒኤስ ሠራተኞች የልጅ መጎሳቆልን ወይም በቸልተኝነት መያዝ ሁኔታ ሕጋዊ ትርጉሙን አሟልቶ ለቀረበ የልጅ መጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት መያዝ ጥርጣሬን መመርመር በሕግ ይጠበቅባቸዋል።

## የልጅ መጎሳቆልና በቸልተኝነት መያዝ ምንድን ነው?

**ብዙ ዓይነቶች የልጅ መጎሳቆልና በቸልተኝነት መያዝ አሉ፣**

በአካል መጎሳቆል በልጁ ላይ በአደጋ ያልመጣን የሰውነት መጎዳትን (የአጥንቶች መሠበር፣ የሰውነት ላይ እብጠት፣ በእሳት የመቃጠል፣ የሰውነት መቀረጥና ሌሎች ጉዳቶችን) ይጨምራል ወይም ማናቸውንም ልጁን አደጋው ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ድርጊቶችን ነገር ግን ባጋጣሚ ሳይሆኑ የቀሩትንም (በመሣሪያ ልጁን የመምታት፣ ልጅ ባለበት ቦታ ሽጉጥ የመተኮስ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶችን) ይጨምራል።

በስሜት ማጎሳቆልም  ልጅን እሱ/እሷ የተወደደ/ች እንዳልሆነ/ች እንዲሰማው/ት ማድረግን ወይም እሱ/እሷ መጥፎ ወይም ዋጋ እንደሌለው/ላት እንዲሰማው/ት ማድረግን (ማንቋሸሽ ወይም ልጅን አሳንሶ ማየት፣ ልጅን ጓደኞች እንዲያበጅ/እንድታበጅ አለመፍቀድ፣ ስድብ የመስደብና ሌሎች ተመሳሳይ ባህርያትን) ይጨምራሉ። በቤተሰብ ውስጥ የሚፈጠሩ ብጥብጦችም በልጆች ላይ የሚደረጉ የስሜት መጎሳቆሎች እንደሆኑ ይቆጠራሉ።



በቸልተኝነት መያዝ  ከአደጋ የተጠበቀ መኖሪያ ቤትን፣ ምግብን፣ ልብስን አለማቅረብ ወይም ሕክምና/የጥርስ ሕክምናን አለማቅረብ እንዲሁም ነብስ ያላወቀ/ች ልጅን ለብቻው/ዋ ጥሎ መሄድ ወይም ልጁን/ጅቷን ሊጠብቅ ለማይችል ሰው ጥሎ መሄድ፣ መኪናው ውስጥ በልጅ መቀመጫ ያልታሠረ ልጅ እያለ ሰክሮ መኪናን መንዳት ወዘተ ሊያጠቃልሉ ይችላሉ። አደገ ያሉ ልጆችንም ለመቆጣጠር አለመቻልም እንደ በቸልተኝነት መያዝ ሊቆጠር ይችላል።

በጾታ የማጎሳቆል  ልጅን ለግብረ ሥጋ ግንኙነት ድርጊት መጠቀምን፣ የግብረ-ሥጋ ተግባርን የሚያሳይ የልጅ ፎቶግራፍን ማንሳት፣ ልጅን ለሽርሙጥና ድርጊት መጠቀም ወይም ሌሎች ከልጅ ጋር የሚደረጉ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነክ ድርጊቶችን ያጠቃልላሉ።

ሌሎች የልጅ መጎሳቆልና በቸልተኝነት መያዝ እንደሆኑ የሚቆጠሩ ድርጊቶች አሉ እናም በእያንዳንዶቹ ሁኔታዎች ላይ የልጁ/ጇ ጤንነት፣ ከአደጋ መጠበቅ፣ ወይም ደህነነት ተገድቶ እንደሆነ ወይም በአደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል መታወቅ አለበት።

## ስለ እኔ ሲፒኤስ የሰማው እንዴት ነው?

ሲፒኤስ ልጆችዎ የሚያስፈልጋቸውን ጥበቃ ወይም እንክብካቤ እንደማያገኙ ሀሳብ የሚያቀርብ ማመልከቻ ደርሶታል።

> "ጉዳዩን ለሲፒኤስ የሚያመለከቱት ግለሰብ ስማቸው በሚስጥር እንዲቀመጥ ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ።"

አንዳንድ ሰዎች እንደ ሐኪሞች፣ ነርሶች፣ አስተማሪዎች፣ የማህበረተሰብ አገልግሎት አማካሪዎች፣ የስነ-አእምሮ ማለሙያዎች፣ መድኃኒት ሻጮች፣ የመዋለ ሕፃናት አገልግሎት አቅራቢዎች፣ ወጣት ጥፋተኞችን ተከታታይ ሕግ አስከባሪዎች፣ የዲኤስኤችኤስ ሠራተኞች፣ የፀባይ ማረሚያ መሥሪያ ቤት ሠራተኞች፣ ባልታወቀ ምክንያት የሚመጣ ሞትን መርማሪዎችና ከፋኛ ከተጎሳቆለ ወይም በቸልተኝነት ከተያዘ ልጅ ጋር የሚኖሩ አዋቂ ሰዎች ጥርጣሬ ያለበትን የልጅ መጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት መያዝን ለሲፒኤስ ወይም ለፖሊስ እንዲያሳውቁ በሕግ ይጠበቅባቸዋል (RCW 26.44.030)።

ማንኛውም ግለሰብ አንድ ልጅ እንደተጎሳቀለ ወይም በቸልተኝነት የተያዘ መሆኑን ካወቀ በቀና ልቡና ጉዳዩን ለሲፒኤስ ወይም ለፖሊስ ሊያመለክት ይችላል። በተንኮል ወይም አውቆ በውሸት ጉዳዩን ማሳወቅ ወንጀል ነው እናም በሕግ ያስከስሳል (RCW 26.44.060(4))። ትዕዛዝ የተሰጣቸው ዘገባ አቅራቢዎች የልጅ መጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት መያዝ ሁኔታ መኖሩን ሲያውቁ ጉዳዩን በ48 ሰዓት ውስጥ ማሳወቁ ይጠበቅባቸዋል።

ጉዳዩን ለሲፒኤስ የሚያመለክቱት ግለሰብ ስማቸው በሚስጥር እንዲቀመጥ ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

## ለልጄ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ሲፒኤስ ምን መብት አለው?

በጥርጣሬ ማመልከቻ የገባበትን የልጅ መጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት መያዝን ሲፒኤስ እንዲመረምር ሕጉ ሥልጣን ይሰጠዋል። የተሟላ ምርመራ ለማድረግ የሲፒኤስ ሠራተኛ ከእርስዎና ከልጅዎ ጋር እንዲሁም ከሌሎች ጠቃሚ መረጃ ሊኖራቸው ከሚችል ሰዎች ጋር ለመነጋገር ይፈልጋል። ሲፒኤስ ለእርስዎ ከመናገሩ በፊትና ያለ እርስዎ ፈቃድ ለልጅዎ ቃለ መጠይቅ ሊያቀርብ መብት አለው። ለልጆቹ በትምህርት ቤታቸው፣ መዋለ ሕጻናት፣ መኖሪያ ቤታቸው፣ ወይም በማንኛውም ለልጁ አመቺና ምቾት ባለው ቦታ ሁሉ ቃለ መጠይቅ ሊደረግላቸው ይችላል።

ልጅዎ በሲፒኤስ ቃለ መጠይቅ ተደርጎለት ከሆነ ወዲያውኑ እንዲያውቁት ይደረጋል።

የልጁን ሰውነት ሁኔታ በመዝገብ ለማስቀመጥ እንዳስፈላጊነቱ ሲፒኤስና ፖሊስ ልጁን ፎቶግራፍ ለማንሳት ሥልጣን አላቸው።

የቤተሰቡን ጥንካሬና በልጁ(ጆቹ) ላይ ሊመጣ የሚችለውን የአደጋ ግምገማ ከመረመረ በኋላ የሕዝብ ሠራተኛው (ጉዳይ አስፈጻሚ) እርስዎና ቤተሰብዎ ነገሮችን ለማቃለል እንዲችሉ ለመርዳት ምን ዓይነት እርዳታ እንዳለ ለመነጋገርና ከልጅዎ ጋር ስላለው ማንኛውም ችግር ለመነጋገር ወደ ቤትዎ ጉብኝት ማድረጋቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ።

## ፖሊስ በጉዳዩ የሚገባው መቼ ነው?

ጥርጣሬ ያለበትን የልጅ መጎሳቆል/በቸልተኝነት መያዝን አስመልክቶ የቀረበ ማመልከቻ ወደ ሲፒኤስ ወይም ወደ ፖሊስ ሊቀርብ ይችላል። ፖሊስም ስለሚደርሰው ማመልከቻ ሁሉ ለሲፒኤስ መንገር ይጠበቅበታል። የሲፒኤስ ሠራተኞችም ሞትን፣ የአካል መጎዳትን፣ የልጅ በጾታ መጎሳቆልን ወይም ሌሎች ወንጀሎችን የሚጠቁሙ ማመልከቻዎችን ሁሉ ለፖሊስ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል።

ልጁን ለአደራ ጠበቂ መስጠት አስፈላጊ ከሆነ ፖሊስ በጉዳዩ ሊገባ ይችላል። ደግሞም የሲፒኤስ ሠራተኛው ደህንነት አስጊ ሁኔታ ላይ እንደሚወድቅ የሚያሳይ ምክንያት በሚኖር ጊዜ ፖሊስ እርዳታ እንዲያደርግ ሊጠየቅ ይችላል።

> “ልጁን ለአደራ ጠበቂ መስጠት አስፈላጊ ከሆነ ፖሊስ በጉዳዩ ሊገባ ይችላል።”

ምንም እንኳን የሲፒኤስ ሠራተኞችና ፖሊስ በሕብረት ቢሠሩም ቀሉ የተለያየ ምርመራ ሊያደርጉ ይችላሉ። ፖሊስ የወንጀለኛ ምርመራ ሲያደርግ ሲፒኤስ ደግሞ የቤተሰብ ግምገማ ያደርጋል። የወንጀለኛነት ክስ ባይቀርብም እንኳን ሲፒኤስ በቤተሰቡ ጉዳይ ውስጥ ሊገባ ይችላል።

## “የአደራ ጠባቂ” ምንድን ነው?



በድንገተኛ ጊዜ  ልጁ በማይቀር አደጋ ላይ ሊወድቅ በሚችልበት ወቅት፡ ወይም በጠና ተጎሳቁሎ ወይም በቸልታ ተይዞ ከሆነ ፖሊስ ልጁን “በአደራ ጠባቂ” ሥር ከ 72 ሰዓት ላልበለጠ ጊዜ (ቅዳሜን፡ እሁድንና የበዓል ቀናትን ሳይጨምር) እንዲቀይ ሊያደርግ ይችላል። ከዚያም የአደራ ጥበቃው ልጁን ወደ ዘመድ ቤት ወይም ፈቃድ ላለው ለማደጎ ለሚመድበው ለሲፒኤስ ይተላለፋል።

ልጁ በአደራ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በ 72 ሰዓት ውስጥ
(ቅዳሜን፡ እሁድንና የባዕል ቀናትን ሳይጨምር) ፍርድ ቤት ጉዳዩን መስማት አለበት።

## ልጄ ለአደራ ጠባቂ ሲሰጥ ምንድን ይሆናል?

ልጅዎ ለአደራ ጠባቂ በሚሰጥበት ጊዜ በተቻለ መጠን ቶሎ በጽሑፍ ማስታወቂያ ይሰጥዎታል። ልጅዎ መቼና ለምን ለአደራ ጠባቂ እንደተሰጠ የሚገልጽልዎት ቅጽ ይሰጥዎታል። ደግሞም መረጃ ማግኘት የሚችሉበትን የሲፒኤስ ሠራተኛ እና/ወይም ቢሮ ስምና ስልክ ቁጥር ይሰጥዎታል። ስለ መጠለያ ጥበቃው ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መቼና የት እንዲሰማ እና ፍርድ ቤቱ የሚመድብልዎትን ጠበቃ እንዴት እንደሚያገኙ ማስታወቂያ ይደርስዎታል።

በመጠለያ ጥበቃ ችሎቱ ላይ ልጅዎ ለምን ከቤትዎ ውጭ መሆን እንደሌለበት ለፍርድ ቤቱ ለማስረዳት ዕድል አለዎት። ዳኛው ወይም የፍርድ ቤት ወኪሉ በእርስዎ ሀሳብ ከተስማሙ ልጅዎ ይመለስልዎታል።

ጉዳይዎን የሰማው የፍርድ ቤቱ ተወካይ ከሆነ የፍርድ ቤት ተወካዩን ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤት ዳኛ እንዲታይልዎት የማድረግ መብት አለዎት። ጉዳዩ እንዲታይልዎ ለማድረግ የፍርድ ቤቱ ተወካይ ውሳኔ ከሰጡበት ጊዜ በ 10 ቀናት ውስጥ ለፍርድ ቤቱ ማመልከቻዎን ማስገባት አለብዎት።

ምንም እንኳን የአደራ ጥበቃው ለፖሊስ ቢሰጥም ዲሲኤፍኤስ የፍርድ ቤት ውሳኔ አስፈላጊ እንዳልሆነ ሊወስን ይችላል። በእነኚህ ጉዳዮች ላይ ያሉት ችግሮች እስኪቃለሉ ድረስ የፈቃደኝነት ምደባ ስምምነት እንዲፈርሙ ሊጠየቁ ይችላሉ። ወይም አገልግሎቶቹ አቤተዎ እንዲሰጡ ሆኖ ልጅዎ(ጆችዎ) ሊመለስልዎት ይችላል።

## ለእኔና ለቤተሰቤ የሚቀርቡ አገልግሎቶች ምንድን ናቸው?

ችግሮችን ለመፍታት ዲኤስኤችኤስ ብዙ አገልግሎቶችን ያቀርባል። አንዳንድ አገልግሎቶች በዲኤስኤችኤስ በቀጥታ ሲሰጡ ሌሎች በማህበረተሰቡ ውስጥ ይቀርባሉ። የሲፒኤስ አገልግሎቶች በነፃ ገቢን ሳያስመለከት ይሰጣሉ። ይሁን እንጂ ቤተሰብዎ ያገልግሎት ሒሳብ ለሚያስከፍል ለሌላ ወኪል ከተላከ የአገልግሎቱን ሒሳብ እንዲከፍሉ ሊጠየቁ ይችላሉ። እንደ ማደጎ ያሉት ከመኖሪያ ቤት ውጭ ለሚሰጡ አገልግሎቶች መክፈል ያለብዎት ወጪ አላቸው።

> “የሲፒኤስ አገልግሎቶች በነፃ ገቢን ሳያስመለከት ይሰጣሉ”

ቤተሰብዎ እንዲያገኘው የሲፒኤስ ሠራተኛ ሊረዱዎት የሚችሉት አንዳንድ አገልግሎቶች እነኚህ ናቸው፥ (ሁሉም አገልግሎቶቹ በየቦታው ላይገኙ ይችለሉ።)

- መኖሪያ ቤት/ልብስ/የተወሰነ የገንዘብ እርዳታ
- የጤና አገልግሎት/የሕክምና እንክብካቤ/የጥርስ ሕክምና
- የቤት ውስጥ መርጃ አገልግሎቶች
- የልጅ ማሳደጊያ(ጥበቃ)
- ለሥራ ቅጥር አገልግሎት

- ስለ የልጅ አስተዳደግ ትምህርት
- የቤተሰብ መምሪያ አገልግሎቶች
- መጉገዣ
- የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች
- የቤተሰብና ጋብቻ ምክር
- የምግብ ባንክ
- የሕግ ነክ አገልግሎቶች
- ሱስ የሚያሲዙ ዕፀዋትንና አልኮሆል መጠጥን በመውሰድ ለመጣ ችግር የመርጃ ፕሮግራም
- የፈቃደኝነት እርዳታ፣ የወላጅ ድጋፍ መስጫ፣ ወላጅነትን አስመልክቶ የሚሰጥ ትምህርት (Parents Anonymous)
- የቤት ብጥብጥ/ለግብረ ሥጋ ግንኙነት መጠቃት መርጃ ፕሮግራም

## አማራጭ እርዳታ መስጪያ ዘዴ (ኤአርኤስ) ምንድን ነው?

በዋሽንግተን ስቴት የሲፒኤስ ዘገባዎች ችግሮችን በመገምገሚያ ኖሙና ይጠናሉ። መረጃዎቹን የሚቀበለው ሠራተኛ የተሰጠው መረጃ ልጅዎ ላይ ሊደርስ የሚችለው ጉዳቱ ደረጃ ቀለል ያለ እንደሆነ ካመለከተ ለልጅዎ ጥበቃና ለስሜት ወይም ሌሎች ዓይነቶች ድጋፎች ለእርሶ መኖራቸውን የሚያረጋግጥ፣ ለእርስዎና ለልጅዎ መከላከያ እንዲያዘጋጁ ለእርስዎ የተለየ የድጋፍ አገልግሎት ለማቅረብ ከሲፒኤስ ጋር ኮንትራት ላለው ወኪል ጉዳይዎ ይተላለፋል።

ከኤአርኤስ አቅራቢ ጋር ተካፍሎ ማድረጉ በፈቃደኝነት ሲሆን አገልግሎቱን አልፈልግም ማለት ይችላሉ። ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜ አገልግሎት አቅራቢዎቹ እርስዎና ልጆችዎ የበለጠ ደስተኛና ምቾት እንዲሰማችሁ የሚያደርጉትን አገልግሎቶች እንድታገኙ ይረዷችኋል። በማህበረተሰብዎ ውስጥ የሚያስፈልግዎትን ዓይነት እርዳታ ካገኙ ከሲፒኤስ

እርዳታውን ማግኘት አያስፈልግዎትም ብለን እናምናለን።

## ሲፒኤስ በሚመረምረኝ ጊዜ ያሉኝ መብቶች ምንድን ናቸው?

በ26.44 RCW ምዕራፍ መሠረት መሥሪያ ቤቱ የልጅ መጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት መያዝ ጉዳይ ላይ ምርመራውን በሚያጠናቅቅበት ጊዜ መሥሪያ ቤቱ ስለ ጉዳዩና የምርመራው ውጤት ወንጀሉን ፈጽመዋል ለተባሉት ሰው/ዎች ማሳወቅ አለበት። ማስታወቂያው በአደራ ደብዳቤ በፖስታ ለግለሰቡ የቅርብ ጊዜ አድራሻ ይላካል።

ሦስት ሊሆኑ የሚችሉ የምርመራ ውጤቶች አሉ። መሠረት ያለው የምርመራ ውጤት ማለት ምርመራውን ያከናወነው ሠራተኛ የልጅ መጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት ተይዟል ስለተባለው አልሆነም ከማለት ይልቅ ሆኗል ብሎ እንዲያስብ በቂ መረጃ አለው ማለት ነው። መሠረት የሌለው ማለት ምርመራውን ያከናወነው ሠራተኛ ተደርጓል የተባለው የልጅ ማጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት መያዝ ሆኗል ከሚል ይልቅ አልሆነም ብሎ ለመውሰድ የሚያስችለው መረጃ አግኝቷል ማለት ነው። ውሳኔ ላይ ለመድረስ የማያስችል ነው ማለት መርማሪው ሠራተኛ የልጅ መጎሰቆል ወይም በቸልተኝነት መያዝ ሆኗል የተባለው መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመወሰን ሳይችል ነው።

መሠረት ባለው ምርመራ መሠረት ተደርጓል ለተባለው የልጅ መጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት መያዝ እርስዎን ይመለከትዎታል ከተባሉ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይና የምርመራውም ውጤት እንዲሻሻል የመጠየቅ መብት አለዎት። ከመሥሪያ ቤቱ የጽሑፍ ማስታወቂያ ባገኙ በ 20 ቀናት ውስጥ መሥሪያ ቤቱ የምርመራውን ውጤት እንደገና እንዲያጠና ሊጠይቁ ይችላሉ። ጥያቄው በጽሑፍ መቅረብ አለበት። ጉዳዩ እንዲጠና የሚያቀርቡት ጥያቄዎ ባስፈላጊው ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ከዚያ በኋላ የምርመራውን ውጤት ሊሞግቱ አይችሉ ይሆናል እናም በፍርድ ቤት ጉዳይዎ እንዲሰማልዎት ወይም የምርመራው ውጤት በፍርድ ቤት እንዲታይ ለማድረግ ምንም መብት አይኖርዎትም።

ጉዳዩ እንዲታይ በጽሑፍ መሥሪያ ቤቱ ጥያቄ ሲደርሰው ጉዳዩን ይመለከተዋል። ተገቢም ከሆነ ውሳኔውን ይቀይረዋል። የአካባቢው ሥራ አስኪያጅ ክፍል ሠራተኞች ጉዳዩን የመመልከት ኃላፊነት አላቸው። ጉዳዩን መመልከቱን ሲያጠናቅቅ መሥሪያ ቤቱ የወኪሉን

መሠሪያ ቤት ውሳኔ በጽሑፍ ያሳውቅዎታል። ማስታወቂያው በአደራ ደብዳቤ በፖስታ ቤት ባለፈው የቅርብ ጊዜ አድራሻዎ ይላካል።

ወኪሉ ጉዳዩን ከተመለከተው በኋላ የቀረበው ዘገባ መሠረት ያለው ከሆነ ውጤቱን ለመሞገት በፍርድ ቤት ጉዳዩ እንዲሰማ ሊጠይቁ ይችላሉ። ጉዳዩ በፍርድ ቤት እንዲሰማ የሚቀርበው ጥያቄ የወኪሉ የጥናት ውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰዎት በሰላሳ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት። ጉዳዩ በፍርድ ቤት እንዲሰማ የሚያቀርቡት ጥያቄ በአስፈላጊው ጊዜ ውስጥ ካልተደረገ ከዚያ በኋላ የምርመራ ውጤቱን ሊሞግቱ አይችሉም፤ እናም ከዚያ ቀጥሎ ወኪሉ ጉዳዩን እንዲመለከተው ወይም በፍርድ ቤት እንዲታይ ወይም ውጤቱ በፍርድ ቤት እንዲታይ ለማድረግ ምንም መብት የለዎትም።

## ሲፒኤስ ጉዳዩን በሚከታተልበት መንገድ ካልተስማማሁ መብቶቼ ምንድን ናቸው?

የሲፒኤስ ተቀዳሚ አሳሳቢ ጉዳይ ከወኪሉ ጋር ጉዳያቸውን የሚያስፈጽሙት ሁሉም ሰዎች በተገቢው መንገድና በክብር መስተናገዳቸውን ማረጋገጥ ነው። ለዚህም ምክንያት የዜጎች አቤቱታ ማቅረቢያ ፖሊሲና የሥራ መመሪያ እንዲሁም አሳሳቢ ጉዳዮች ሥርዓት ባለውና በተገቢው መንገድ በሰዓቱ መታየታቸውን ለማረጋገጥ መንገድ የሚያወጣ ልዩ መግለጫ ጽሑፍ አለን። የእርስዎ ጉዳይ የተመራበትን መንገድ አስመልክቶ የሚቀርቡ አሳሳቢ ጉዳዮች በእርስዎ፣ በልጅዎ፣ በቤተሰብዎ አባል ወይም በሌላ ስለ ሁኔታው ዕውቀት ባላቸው ሰው ሊቀርብ ይችላል።

ጉዳዩ በሲፒኤስ ስለተመራበት ወይም ስለሚመራበት መንገድ አቤቱታ ወይም አሳሳቢ ጉዳይ ካለዎት በቅድሚያ አሳሳቢ ጉዳይዎን ለተመደቡት የሕዝብ ሠራተኛ (ጉዳይ አስፈጻሚ) መግለጽ አለብዎት። ይህ ችግሩን ሊያቃልለው ካልቻለ በቀጥታ የሠራተኛውን አለቃ ሊያነጋግሩ ይችላሉ። ይህ ጉዳይ በአለቃው ሊፈታ ካልቻለ የአካባቢውን አስተዳዳሪ ሊጠይቁ ይችላሉ፤ ከዚያም በኋላ የበላይ የአካባቢ አስተዳዳሪውን ሊጠይቁ ይችላሉ። በማንኛውም ጊዜ ችግሩን

ለመፍታት እርዳታ ለማግኘት ለአባል ግንኙነት ቢሮ በ 1-800-723-4831 ሊደውሉ ይችላሉ።

ማንኛውም ግለሰብ ለቤተሰብና ልጆች አቤቱታ ሰሚ ቢሮ በ 1-800-571-7321 ደውሎ አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል። ቢሮው ከዲኤስኤችኤስ የተለየ ሲሆን በማንኛውም የዋሽንግተን ስቴት ዜጋ የልጆች አስተዳደር ስለተወሰደው እርምጃ የቀረበውን አሳሳቢ ጉዳይ የመመርመር ሥልጣን አለው። አቤቱታ ሰሚው በጉዳዩ ከመግባቱ በፊት የአቤቱታ መፍቻ የውስጥ የሥራ ቅደም ተከተል መወሰዱን ይጠይቃል።

## ከመኖሪያ ቤት ውጭ ምደባ ምንድን ነው?

ብዙውን ጊዜ ለሲፒኤስ ዘገባ የቀረበባቸው ልጆች ከቤታቸው አይወሰዱም። ልጆች ከወላጆቻቸው የሚወሰዱት ወዲያውኑ ከሚመጣ ጉዳት ወይም ከማያቋርጥ መጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት መያዝ ለማዳን አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ ብቻ ነው።

አብዛኛውን ጊዜ ተገቢ የሆነ ዘመድ ልጁን የመመደቢያ ተመራጭ ቦታ ነው። ተገቢ የሆነ ዘመድ ካልተገኘ ልጁ ፈቃድ በተሰጠው የማደጎ ቤት ይመደባል። የማደጎ ወላጆች ለልጁ የዕለት ከዕለት እንክብካቤ ሲያደርጉ ልጁን ለመንከባከብ የሚወጣውን ወጪ ለመሸፈን ወርሐዊ የወጪ መተኪያ ክፍያ ያገኛሉ። ልጁና የማደጎ ወላጆቹ ልጁ ከእነሱ ጋር እስካለ ድረስ ለዚሁ ጉዳይ በተመደበ የሕዝብ ጉዳይ አስፈፃሚ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል።

> “አንዳንድ ልጆች ጽኑ ችግር ስላለባቸው በቤተሰብ ዓይነት ኑሮ መኖር አይችሉም።”

አንዳንድ ልጆች ጽኑ ችግር ስላለባቸው በቤተሰብ ዓይነት ኑሮ መኖር አይችሉም። እነኝህ ልጆች በማህበር መኖሪያ ቤት ወይም በማስታመሚያ ማዕከል ውስጥ ሊመደቡ ይችላሉ። የዚህ ዓይነቶቹ ምደባዎች አስቸጋሪ በሆነ ባህርይ ወይም የአእምሮ ጤና ችግር ያለባቸውን ልጆች ለማስተናገድ በተሻለ ሁኔታ የተዘጋጁ ናቸው።

## “ጥገኝነት” ምንድን ነው?

በጣም የጸና ችግር ባለበት ጉዳይ ላይ መሥሪያ ቤቱ ወይም ሌላ ማንኛውም ግለሰብ የሚከተሉትን በመጥቀስ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ሊያስገባ ይችላል፡

- ልጁ ያለጠባቂ ተትቶ ነበር
- ልጅ ተገሳቁሎ ወይም በቸልተኝነት ተይዞ ነበር
- ለልጁ እንክባካቤ ማድረግ የሚችል ወላጅ፡ አሳዳሪ፡ ወይም አዳሪ ጠበቂ የለውም ነበር

ከእነኝህ ምክንያቶች አንዱ የጥገኝነትን ሁኔታ ያሟላ እንደሆን ለመወሰን ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ይሰማል። ደግሞም ፍርድ ቤቱ ልጁ/ልጅቷ በቤቱ/ቷ ውስጥ መኖር እንዳለበት/ባት ወይም ከመኖሪያ ቤቱ/ቷ ውጭ መመደብ እንዳለበት/ባት እንዲሁም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በሚመለከትበት ወቀት ልጁን/ልጅቷን የሚቀጣጠረው ማን እንደሆነ ውሳኔ ይሰጣል። ይህ የፍርድ ቤት ጊዜያዊ ትዕዛዝ “ጥገኝነት” ይባላል።



ፍርድ ቤቱ ቤተሰቡን ለማገናኘት ያወጣው ዕቅድ በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚካሄድ ለማየትና ፍርድ ቤቱም በጉዳዩ ላይ የመግባቱ ሁኔታ መቀጠሉ አስፈላጊ መሆኑን ለማየት በየስድስት ወራት የጥገኝነቱን ጉዳይ ለመስማት ችሎት ይቀመጣል።

## ወላጅ እንደመሆኔ ልጄ ከመኖሪያ ቤት ውጭ ለሚደረግለት ጥበቃ ከተመደብ ወይም ጥገኛ መሆኑ ከታወቀ ያሉኝ መብቶች ምንድን ናቸው?

ፍርድ ቤቱ በሌላ መልክ የፍርድ ትዕዛዝ ካልሰጠ በስተቀር ወላጆች ሌሎች ተጨማሪ መብቶች አሏቸው።

ልጅዎ በአደራ ጠባቂ ሥር ሲመደብ ጊዜ ሳይወስድ ስለ ሁኔታው የማወቅና ለምን ልጁ እንደተመደበ መረጃ የማግኘት መብት አለዎት።

ልጅዎ ከመኖሪያ ቤቱ ውጭ ከተመደበ (በማደጎ ቤት፣ በማህበር መኖሪያ ቤት፣ በማዕከላት) እንዳይገበኙ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ካልሰጠ በስተቀር የመጎብኘት መብት አለዎት። አብዛኛውን ጊዜ የፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ በየስንት ጊዜ መጎብኘት እንደሚገባዎትና የት ቦታ እንደሚገበኙ ይወስናል።

ሁል ጊዜም ቢሆን የመጎብኘት መብትዎን የሚወስነውን ወይም የሚከለክለውን ውሳኔ ሊቃወሙ ይችላሉ።

ሲፒኤስ ባለው ሥልጣን ሁሉ የልጁን የጤና ሁኔታና ዕድገት፣ የትምህርት ቤት ሁኔታ እንዲሁም ባህርይ እንዲያውቁ ጥረት ያደርጋል። ይህ እንዲፈጸም ለሲፒኤስ ሠራተኛ የኑሮ ሁኔታዎችዎን ማሳወቅዎ መቀጠል አለበት።

ልጅዎ ከመኖሪያ ቤቱ ውጭ ከተመደበ በኋላ እቤቱ ተመልሶ እንዲገባ ለማድረግ እርስዎ ምን ማድረግ እንደሚጠበቅብዎት የማወቅ መብት አለዎት።

> “መረታት ለሚያስፈልጋቸው ችግሮች እርዳታ እና/ወይም ምክር የማግኘት መብት አለዎት።”

የእርስዎንና የልጅዎን ጉዳይ የሚመለከት ለውጥ ሊደረግ እየታሰበ ከሆነ በጉዳዩ የሃሳብ ተካፋይ የመሆን መብት አለዎት።

መረታት ለሚያስፈልጋቸው ችግሮች እርዳታ እና/ወይም ምክር የማግኘት መብት አለዎት።

በቅድሚያ የማወቅና እንዲሁም ልጅዎን በሚመለከት ወይም የወላጅነትዎን መብት በሚነካ ማንኛውም የፍርድ ቤት ችሎት ላይ (ፍርድ ቤቱ በአስቸኳይ ሁኔታ እርምጃ ካልወሰደ በስተቀር) የመካፈል መብት አለዎት።

በቂ ምክንያት ኖሮ የ 72 ሰዓቱ ችሎት ላይ መካፈል በማይችሉ ጊዜ ፍርድ ቤቱ የመጠለያ እንክብካቤ ጉዳይን አስመልክቶ ችሎት እንዲቀመጥ የመጠየቅ መብት አለዎት።

ጉዳይዎ በሚሰማበት በእያንዳንዱ ጊዜ ላይ በቀረበው ማስረጃ መሠረት ብቻ ለአድሎ ባልተጋለጠ ዳኛ ወይም መርማሪ ፍርዱን የማግኘት መብት አለዎት።

ፍርድ ቤቱ ጉዳይዎን ለመመልከት ተካፋይ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ ጠበቃ የመያዝ መብት አለዎት። ጠበቃ ለመያዝ የገንዘብ አቅም ከሌለዎት ፍርድ ቤቱ የሚመድብልዎትን ጠበቃ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ የሲፒኤስ ሠራተኛ መረጃ ይሰጥዎታል።

ሁሉም ባለጉዳዮች በሚመርጡት ቋንቋና ባህላቸውን በሚያከብር መንገድ አገልግሎቶችን የማግኘት መብት አላቸው።

## የልጆ መብቶች ምንድን ናቸው?

**ልጅዎም መብቶች አሉት/አሏት እነሱም፡**

- ፍላጎቱን/ቷን የሚያሟላ ምግብ፡ መጠለያና ልብስ የማግኘት መብት አለው/አላት።
- ጥበቃ እንዲደረግለት/ላት እና ከጉዳት፡ ከአስጨናቂ ነገር፡ ከአደጋ፡ ከመቁሰልና በቸልተኝነት ከመያዝ ነፃ የመሆን መብት አለው/ላት።
- የግል ስሜታቸው የመጠበቁ መብት።
- የጤና እንክብካቤ የማግኘት መብት፡ የጤና ምርመራ ፣ ለጥርስ ሕክምና እንዲሁም ለስሜት ነክ ሁኔታዎች ሕክምናን ጨምሮ
- በማንኛውም የፍርድ ቤት ድርጊት ጊዜ የልጁን/የልጅቷን መብት የመጠበቅ። "የልጅ መብት ጠባቂ" የተባለ ግለሰብ የልጁን መብት ለመጠበቅ እንዲረዳ በፍርድ ቤት ሊመደብ ይችላል። ይህ የሚሆነው ፍርድ ቤት የተኛውም ዓይነት እርምጃ ከወሰደ ነው።

## ከእኔ የሚጠበቀው ምንድን ነው?

**የተወሰኑ ኃላፊነቶች አለብዎት፡**

- ለልጅዎ አስፈላጊ ልብሶችና የግል መገልገያ እቃዎች (ቢጃማ፡ መጫወቻ አሻንጉሊቶች፡ ወይም ሌሎች ዕቃዎችን) የማቅረብ፡ ልጅዎ ከመኖሪያ ቤቱ/ቷ ውጭ ከሆነ/ች በበለጠ ምቾት እንዲሰማው/ት ለመርዳት።
- ልጅዎን በየጊዜው የመጎብኘት፡ ከሲፒኤስ ሠራተኞች ጋር በተስማሙበት ጊዜና ቦታ ላይ

ለጉብኝቱ መገኘት ካልቻሉ ለሲፒኤስ ሠራተኛው በቅድሚያ ማሳወቁ የእርስዎ ኃላፊነት ነው።

- የልጁን/ጅቷን የወደፊት ኑሮ በማቀድ ላይ ከሲፒኤስ ሠራተኛ ጋር አብሮ መሥራት፣ እርስዎ መውሰድ የሚያስፈልገዎትን እርምጃዎችንም ጨምሮ።
- ለልጁ መጎሳቀል ወይም በቸልተኝነት መያዝ ሁኔታ ምክንያት የሆኑትን ችግሮች ለመፍታት መጣር። የሲፒኤስ ሠራተኛው እና/ወይም ፍርድ ቤቱ ለዚህ ችግር እርዳታ እንዲያገኙ ከመራዎት መመሪያውን የመከታተል ወይም ስለ አሳሳቢ ጉዳዮችዎ ከጉዳይ አስፈጻሚዎ ጋር መነጋገር አለብዎት።
- በሕይወትዎ ላይ ለሚመጡት ለውጦች ለጉዳይ አስፈጻሚው በየጊዜው ማሳወቅ፣ ለውጦቹም እንደ አዲስ አድራሻ ወይም የስልክ ቁጥር ለውጥ፣ የሥራ ሁኔታ ለውጥ፣ የጋብቻ/የፍቺ ወይም ሌሎች ለልጅዎ የተያዘውን ዕቅድ የሚነኩ ለውጦች ዓይነቶች ናቸው።
- ከሲፒኤስ ሠራተኞችና ከሌሎች እርዳታ ከሚሰጡ ባለሙያዎች ጋር ያለዎትን ቀጠሮ ማክበር። ቀጠሮዎን ማክበር ካልቻሉ ወይም መሰረዝ ካለብዎት ለሲፒኤስ ሠራተኛው በቅድሚያ ያሳውቁ።
- ስለ ልጅዎ መረጃ የማቅረብ፣ የሕክምና፣ የትምህርት ቤት ሁኔታ፣ ወይም ሌሎች ለልጅዎ የወጣውን ዕቅድ ሊነኩ የሚችሉ መረጃዎችን ጨምሮ።
- ስለ ልጅዎ እንክብካቤና ስለ ጉዳዩ ሂደት ከሲፒኤስ ሠራተኛ ጋር የመነጋገር።
- ለልጅዎ እንክብካቤ ለማድረግ ለውጣው ወጪ አስተዋጽኦ የማድረግ።

## ልጄን መልሼ ማግኘት የምችለው እንዴት ነው?

ልጅዎ ከአደጋ የተጠበቀ እስከሆነ ድረስ እቤትዎ እንዲያቆዩት ሲፒኤስ ይፈልጋል። ሲፒኤስ ልጁን ከመኖሪያ ቤቱ ውጭ ለመመደብ እርምጃ የወሰደው በቤቱ ውስጥ የተፈጠረው ሁኔታ ከፍተኛ አደጋ የሚያመጣ ስለሆነ ወይም ልጁ ለአደጋ ስለተጋለጠ ነው። ግልባጩ የደረሰዎት የጥገኝነት ማመልከቻ ጉዳይ አስፈጻሚው ልጅዎን አደጋ ላይ ይጥለዋል ብለው ያሰቡትን

> "ልጅዎ ከአደጋ የተጠበቀ እስከሆነ ድረስ እቤትዎ እንዲያቆዩት ሲፒኤስ ይፈልጋል።"

ሁኔታ ይገልጻል። ምን እንደሚል ካልገባዎት ጉዳይ አስፈጻሚዎንና ጠበቃዎን ስለ ማመልከቻው እንዲያብራሩልዎት ይጠይቁ። ልጅዎ እንዲመለስልዎት በማመልከቻው ላይ የተገለፁት ሁኔታዎች መፍትሄ ማግኘት አለባቸው።

**ይህን ለማከናወን ጥሩዎቹ መንገዶቹ የሚከተሉት ናቸው፣**

- የልጅዎ ጉዳይ በፍርድ ቤት በሚሰማበት ጊዜ ሁሉ ፍርድ ቤት መገኘት። ፍርድ ቤት ካልተገኙ ዳኛው አለመገኘትዎን በልጅዎ ላይ ስለሚሆነው ነገር ግድ የለዎትም ብለው ሊያስቡ ይችላሉ።
- የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ማክበር። ልጅዎን(ችዎን) አስመልክቶ ከፍርድ ቤት የተሰጠው ማንኛውንም ትዕዛዝ በተለይ ማሟላት የሚያስፈልግዎትን የጉዳይ ዕቅድ ይጨምራል። ፍርድ ቤቱ በኀይት መቆጣጠሪያ ትምህርት ላይ ወይም ሱስ ለሚያሲዝ ዕጽ ሕክምና እንዲካፈሉ ትዕዛዝ ከሰጠዎት ትዕዛዙን ያክብሩ። ምንም እኳን አያስፈልገኝም ብለው ቢያስቡም ቀሉ። ከትምህርቱ ወይም ከሕክምናው ስለራስዎ ሊማሩ በሚችሉት ነገር ሊደነቁ ይችላሉ።
- ልጅዎ እቤትዎ መምጣት ይችል ዘንድ ሁሉን ነገር ከአደጋ የተጠበቀ ያድርጉት። ይህ ማለት እቤትዎ ያለ ሰው ከቤትዎ እንዲለቀ መጠየቅ ሊሆን ይችላል። ወይም ያለብዎትን ችግር መፍታት ሊሆን ይችላል። ወይም የአኗኗር ሁኔታዎን ለማሻሻል እርምጃዎችን መውሰድ ሊሆን ይችላል። ፍርድ ቤቱ ቤትዎ ከአደጋ የተጠበቀ እስኪሆን ድረስ ልጅዎ እቤትዎ እንዲመጣ አያደርግም።

## ጠበቃ ያስፈልገኛልን?

ከፈለጉ በማንኛውም ጊዜ ጠበቃ ለመያዝ ነፃ ነዎት። ይሁን እንጂ የጥገኝነት ማመልከቻ እስካልገባ ድረስ ፍርድ ቤቱ የሚመድብልዎትን ጠበቃ አያገኙም።

የጥገኝነት ማመልከቻ ከገባ ጠበቃ ያስፈልግዎታል። ጠበቃ ለመያዝ የገንዘብ አቅምዎ ካልፈቀደ ፍርድ ቤቱ ይመድብልዎታል። ልጅዎ በአደራ ጠባቂ ሥር ከተመደበ የሚደርስዎት የጽሑፍ ማስታወቂያ እንዴት ጠበቃ መጠየቅ እንደሚቻል ይገልጽልዎታል። ካልገባዎት ለሲፒኤስ ሠራተኛ ወይም ለወጣት ልጆች ፍርድ ቤት ይደውሉ።

ጠበቃዎ በፍርድ ቤት የእርስዎን ጥቅም ይወክላል። በእያንዳንዱ የፍርድ ቤት ችሎት ላይ ጠበቃዎ በደንብ ሊወክልዎት ይችሉ ዘንድ ከእርሱ/ከእርሷ ጋር በቅድሚያ መወያየትዎን ያረጋግጡ። እርስዎና የልጅዎ ሌላኛው ወላጅ ካልተጋባችሁ ወይም ተለያይታችሁ የምትኖሩ ከሆነ የተለየ ጠበቃ ለሁለታችሁም ሊመደብ ይችላል።

የልጅዎን ዋናዎቹን ጥቅሞች እንዲወክል "የልጅ መብት ጠባቂ" ሊመደብ ይችላል። እኚህ ግለሰብ ከእርስዎ ጋር ለመነጋገር ይፈልጉ ይሆናል። ከሆነም ስለ ልጁ የሚያውቁትን ከነገሩ እሱ/እሷ በተሻለ መንገድ ልጅዎን እፍርድ ቤት ሊወክሉ ይችላሉ።

የሲፒኤስ ሠራተኛዎ ከአቃቤ ሕጉ ቢሮ በሚመደበው ጠበቃ ይወከላሉ።

## ለልጄ የወደፊት ኑሮ ዕቅድ የማወጣው እንዴት ነው?

ቋሚ የሆነ መኖሪያ ቤት ማግኘት ለልጁ በጣም አስፈላጊ ነው። እርስዎ ልጅ በነበሩ ጊዜ በማደጎ ቤት ኖረው ከሆነ ወይም ከዘመድ ወደ ዘመድ ቤት እያሉ ኖረው ከነበረ ይህ ለልጅ ምን ያህል ዋና ነገር እንደሆነ ሊገባዎት ይችላል።

ሲፒኤስም ቋሚ መኖሪያ ቤት ለልጅ ምን ያህል ዋና ነገር እንደሆነ ያውቃል። ልጅን ከእሱ/ከእሷ ቤተሰብ መውሰዱ ብዙውን ጊዜ ጊዜያዊ ጉዳይ ነው። የሲፒኤስ ግብ ጊዜያዊ ምደባውን ማቆምና ልጁ በራሱ/በራሷ ቤት ከአደጋ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲኖር ማረጋገጥ ነው።



ከሲፒኤስ ጋር ዕቅድ ለማውጣትና ለመጻፍ አብሮ በመሥራት ልጅዎን ሊረዱ ይችላሉ። ይህ ዕቅድ እርስዎና ሲፒኤስ የተወያያችሁባቸውን ችግሮች መዘርዘር

አለበት። ዕቀዱ ችግሮቹን ለማስተካከል ምን መደረግ እንደሚያስፈልገው፣ ማን ምን ማድረግ እንዳለበት፣ እንዲሁም ይህ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ መጥቀስ አለበት።

## የወላጅነት መብቶች መቀም" ምንድን ነው?

> "የወላጅነት መብት መቀም ማለት ወላጅ ለልጁ ምንም ዓይነት መብቶች ወይም ኃላፊነቶች አይኖሩትም ማለት ነው።"

የወላጅነት መብት መቀም ማለት ወላጅ ለልጁ ምንም ዓይነት መብቶች ወይም ኃላፊነቶች አይኖሩትም ማለት ነው። ወላጁ ልጁን ለማየት ወይም ለመጎብኘት፣ የልጁ ጠባቂ ለመሆን፣ የልጁን የወደፊት ኑሮ ለመወሰን ምንም ዓይነት ሕጋዊ መብት የለውም። ፍርድ ቤቱ የወላጁን ለልጁ ወይም ለልጇ ያላቸውን ሕጋዊ መብቶች የማቀም ሥልጣን አለው።

በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ "የወላጅነት መብትን ማስተላለፍ" የተባለ ሕጋዊ ሰነድን በመፈረም አንድ ወላጅ በፈቃደኝነት ልጁ ለጉዲፈቻ እንዲሰጥ ይተዋል። ይህንን ሰነድ መፈረሙ በጣም ጥብቅ ጉዳይ ነው። እናም በጥንቃቄ ሊታሰብበትና ከሲፒኤስ ጉዳይ አስፈጻሚና ከጠበቃ ጋር ውይይት ሊደረግበት ያስፈልጋል።

**የሚከተሉት ሲሆኑ ፍርድ ቤቱ የወላጁን መብቶች ያለፈቃድ ሊያቀም ይችላል፣**

- ፍርድ ቤቱ ጥገኝነት እንዳለ ሲወስን
- ፍርድ ቤቱ ለጥገኝነቱ መንስኤ የሆኑትን ችግሮች ለማስተካከል አገልግሎቶች እንዲሰጡ አዞ ነገር ግን ችግሮቹ አሁንም ካሉ
- ልጅዎ ከቤቱ ውጭ ለሚደረግለት ጥበቃ ለ 12 ወራት ሄዶ ከነበረና እርስዎ ግን በቅርብ ጊዜ ውስጥ ልጅዎ ወደ ቤቱ በደህና እንዲመለስ ለማድረግ ምንም ዓይነት በቂ እርምጃ ካላሳዩ።
- በፍርድ ቤት የታዘዙት አገልግሎቶች ቀርበውና ተሰጥተው ከሆነ።
- ልጁ ወደ ቤቱ መመለስ እንዲችል ያሉት ሁኔታዎች የሚሻሻሉበት ዕድል ትንሽ ከሆነ፣ እንዲሁም
- በወላጁና በልጁ መሃከል ያለው ግንኙነት መቀጠሉ ለልጁ ቋሚ መኖሪያ ቤት ለማግኘት የበለጠ አስቸጋሪ ካደረገው።

የወላጁ መብት በሚቀምበት በማንኛውም ጊዜ የዲሲኤፍኤስ ሠራተኛ ለልጁ ቋሚ መኖሪያ ቤት ለማግኘት ጥረት ያደርጋል።

## በጉዳዩ ውሳኔዎች ላይ ከሲፒኤስ ጉዳይ አስፈፃሚ ጋር ስምምነት ካልተደረሰ አንድ ግለሰብ ምን ማድረግ ይችላል?

ከሲፒኤስ ሠራተኛ ጋር የሚደረግ ግልጽ ውይይት ብዙዎቹን ውዝግቦች ሊፈታ ይችላል። ይሁን እንጂ ውዝግቦቹ በዚያ ደረጃ ሊፈቱ ካልቻሉ ማንኛውም ግለሰብ ቢሆን በዚህ መጽሔት ውስጥ ቀደም ብሎ የተገለፀውን አቤቱታ የማቅረቢያውን ተግባር መጀመር ይችላል።

የጥገኝነት ሁኔታ ካለበት ወላጆችና ልጆቹ ስለ ውዝግባቸው ለጠበቃቸው መንገር አለባቸው። የሲፒኤስ ሠራተኛ ይህን መረጃ ለመሥሪያ ቤቱ ጠበቃ ይሰጣል።

**በእነኝህ ድርጊቶች ምንም መፍትሄ ካልተገኘ ማንኛውም ግለሰብ ለሚከተሉት ሊደውል ይችላል፡**

- ለ The Office of the Family and Children's Ombudsman በ 1-800-571-7321 ወይም ለ Children's Administration Office of Constituent Relations በ 1-800-723-4831 ወይም (360) 902-8061

- ግለሰቡ ችግሩ የግል መብት መጣስ ምልክት ነው ብሎ ካመነ ሌሎች ወኪል መሥሪያ ቤቶች ሊደወልላቸው ይቻላል።

- Office for Civil Rights, United States Department of Health and Human Services, 1-800-362-1710, ቲዲዲ (206) 615-2296

- Washington State Human Rights Commission; 1-800-605-7324 ለሲያትል፡ 1-800-233-3247 ለኦሊምፒያ፡ 1-800-662-2755 ለያከማ

- Division of Access and Equal Opportunity, Washington State Department of Social and Health Services; 1-800-521-8060, ቲዲዲ 1-800-521-8061

ሁሉም ፖሊሲዎች፣ የአሠራር ቅደም ተከተሎቹና የዲሲኤፍኤስ የሥራ መመሪያዎች የሕዝብ ሰነዶች ሲሆኑ በአካባቢ ቢሮ ሊነበቡ ይችላሉ። ወቅታዊ የሆኑት መመሪያዎች ተዘጋጅተው እንዲቀመጡና ጥያቄዎችዎን የሚመልስ ሰው እንዲገኝ ቀጠሮ ለመያዝ እባክዎን አስቀድመው ይደውሉ።

የዋሽንግተን የተሻሻለው ኮድ (RCW) የተባሉት ሕጎች በዋና ዋና ቤተ-መጽሐፍት ለጥናት የሚነበቡ መጽሐፍት ካሉበት ክፍል፣ በጠበቃዎ በኩል፣ ወይም አንዳንዴ ከካውንቲው ፍርድ ቤት ውስጥ ይገኛሉ። ሲፒኤስን የሚመለከቱት ክፍሎች በምዕራፍ 13.3፣ 26.44፣ እና 74.13 ውስጥ ይገኛሉ።

በሲፒኤስ ምርመራ ውስጥ በቀጥታ የተካፈሉ ግለሰቦች ቀጠሮ በመያዝ ወይም በአካባቢው



የዲሲኤፍኤስ ቢሮ በኩል በመጠየቅ የግላቸውን መዝገብ ማየት ይችላሉ። ባለጉዳዮች ከማየታቸው በፊት አንዳንድ መረጃዎች ከእነዚህ መዝገቦች ውስጥ መሰረዝ አለባቸው።

## ልዩነት ያለማድረግ ፖሊሲ

ማንኛውም ሰው በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ በብሔር፣ በዕምነት፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በዕድሜ፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ ወይም አካል ጉዳተኛ የሆነው ሰው በሰለጠነ መሪ ውሻ ወይም አገልጋይ ውሻ በመጠቀሙ መሠረት ልዩነት እንዳይደረግበት፣ ከተካፋይ እንዳይወገድ፣ ወይም ከማንኛውም መርሐግብር ወይም ድርጊት ወይም ኮንትራት ጥቅም እንዳይከለከል የልጆች አድተዳደር ፖሊሲ ይገልፃል። በአካል ለተጎዱ ሰዎች ተገቢ የሆነ መስተንግዶ፣ የቃል አስተርጓሚዎች፣ በተለየ መልክ መርጃ ቁሳቁሶችንም ጨምሮ በጥያቄ ይቀርባሉ።

- በልጆች አስተዳደር (Children's Administration) ልዩነት ተደርጎብናል ብለው የሚያምኑ ባለጉዳዮች ከሚከተሉት ውስጥ ለአንዱ ወኪል መሥሪያ ቤት አቤቱታቸውን ማቅረብ

ይችላሉ፣

- Office for Civil Rights, United States Department of Health and Human Services, 1-800-362-1710, ቲዲዲ (206) 615-2296
- Washington State Human Rights Commission; 1-800-605-7324 ለሲያትል፣ 1-800-233-3247 ለኦሊምፒያ፣ 1-800-662-2755 ለያከማ
- Division of Access and Equal Opportunity, Washington State Department of Social and Health Services; 1-800-521-8060, ቲ.ዲ.ዲ. 1-800-521-8061

Washington State
DEPARTMENT OF
SOCIAL & HEALTH
SERVICES

DSHS 22-484(X) AM (Rev. 2/00)